ከጎቦ ዉቃው ጥቅምት 14/2000
ኖቫ-ስኮሻ ካናዳ

# “ብርቱካኔ-የሎሚ-ሽታ

ብርቱካኔ የሎሚ ሽታ
ያ ብርሃኑ ምን አለሽ ማታ?

ምንም፤ምንም፤ ምንም አላለኝ
ቅንጅት ፈቶ ልውሰድሽ አልኝ

ይወስድሻል፤ ቅንጅት ፈቶ
ምሎልናል፤ በመለስ ፎቶ

ማላ፤ማላ የባንዳ ማላ
ትግቶታል፤ እንደ ጉሽ ጠላ

ከቤቴ በላይ “ፅጌ” ሰፍሮ!
. . .”መዋ” ሰፍሮ!
የለችም ብሎ ሄዶ በሮ!
. . . ሄዶ በሮ!

እሱን ያብረው ያክንፈው፤ያክንፈው፤
የሻውል ሃሞት ያስጠጣው!
. . . ያስጠጣው!
የ”ታዬ” ሃሞት መራራ ነው!
. . . መራራ ነው!
የሻውል ልቡ ተራራ ነው!
. . . ተራራ ነው!

አፄ-ቤት ውሎ ሲመለስ፤
“መዋ-ለፅጌ” ሲያለቅስ፤
“ነጋ” ጥግ ይዞ ሲቀድስ፤
“ቀና” አንገቱን ሲነቀስ።

ከዚህ በላይ የለም መርከስ
ሳይመሽ ብርቱካን ትመለስ
ያለ መንደሩአ አትደንስ!

ቸር ይግጠመን

ከዉቃው